የሰ/መ/ቁ 42361

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ትዕግስት ንጉሴ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ኤስ.ኦ.ኤስ.ኢንፋንት ኢትዮጵያ - ነ/ፈጅ አያንቱ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የአሁኗ አመልካች ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የስራ ውሉን አቋርጧል በማለት የመሰረቱት ክስ ከታየ በኋላ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ እርምጃው ሕገ-ወጥ በመሆኑ አመልካችን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው በመ/ቁ 38316 ከወሰነላቸው በኋላ አመልካች ወደ ስራ ቢመለሱ ከተጠሪ ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት እንደማይኖራቸው ገልፀው ለሕገ-ወጥ ስንብት የሚከፈሉ ክፍያዎችንና የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት የአፈፃጸም ማመልከቻ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የካሳ፣ ስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ ሠጥቶ የፕሮቪደንትና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያን ግን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘትም አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ታህሣስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 4(አራት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪም በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመሰረቱት ዋና ክስ ላይ የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ ማንሳታቸውን ተጠሪ ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ፕሮቪደንት ፈንድ ያለመኖሩንና ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ለፕሮቪደንት ፈንድ የተቆረጠ ምንም ገንዘብ ያለመኖሩን በመግለፅ መከራከሩን ነው፡፡ በዚህ በግራ ቀኙ ክርክር ማስረጃ ተመርምሮ ተገቢው ዳኝነት አልተሠጠበትም፤ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የአሳረፈው የስራ ውል መቋረጡ ሕገ-ወጥ በመሆኑ ላይ ሲሆን፤ የሠጠውም መፍትሔም (Relief) አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ የሚል የነበረ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ አመልካች በፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሠረት ወደ ስራ መመለሱን በመተው በምትኩ የተለየዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

በመሠረቱ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚል ውሣኔ ያገኘ ሠራተኛ ከዚህ ውሣኔ በኋላም ቢሆን ወደ ስራ ለመመለስ ፍላጎት ከሌለው ካሣ ተከፍሎት ከስራ እንዲሰናበት በማድረግ የሥራ ክርክሩን የሚወስነው አካል ሊወሰን እንደሚችል

አዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 43(3) ስር አስቀምጧል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለውም ቀድሞ የተወሰነ ውሣኔ ከመፈጸሙ በፊት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል ተብሎ የተወሰነው ውሣኔ ከመፈፀሙ በፊት በምትኩ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለውኝ ልሰናበት የሚል የአፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረባቸው ግራ ቀኙን ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ የፕሮቪደንት ክፍያ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ጥያቄውን ያልተቀበሉት ወደ ስራ የመመለስ አማራጭ ቀርቶ በአዋጁ አንቀፅ 43/3/ መሰረት በካሳ ሠራተኛው እንዲሰናበት ሲደረግ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚችለው በዋናው የፍሬ ነገር ክርክር ውሳኔ ያላገኘ ክፍያ አይደለም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚገባው ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓቱ ከቁጥር 371 ጀምሮ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ሳይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነቶች መካከል ወደ ስራ የመመለስ ጥያቄ ላይ ብቻ ውሳኔ ከተሠጠ እና ሰራተኛው ወደ ስራ መመለስ ሳይፈልግ ሲቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሳኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠይቅ እንደሚችል ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄው ሲቀርብ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበ ማስረጃ በተገቢው መንገድ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ነው፡፡ የአመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ በተጠሪ በኩል ክርክር የቀረበበት ነው፡፡ ወደ ስራ እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈል የሚወሰንበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ እንዲሁም የፕሮቪደንት ፈንድ እንደሌሎች ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመነጩ የመብት ጠያቂዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ስር በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ ገደቦች የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ድንጋጌ ስር በተመለከተው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ የሚታገድ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሠ/መ/ቁ 32545 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፕሮቪደንት ክፍያ ጥያቄ በአፈፃፀም መዝገብ ሳይሆን ሌላ የዋና ክርክር መዝገብ ከፍተው ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42459 ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ እና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 68296 መስከረም 10 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ